# የፈጣሪ ስሞች
(שם האלוהים)

"የፈጣሪ ስሞች" ተብላ በፓስተር ኮከብ ገዳሙ የቀረበችው መጽሐፍ የኤሎሂምን እውነተኛ ስሙን፣ ባህርይውን፣ ማንነቱን፣ ሁሉን ቻይነቱን ፣ ዘላለማዊነቱን፣ የበላይነቱንና ወዘተ እንድረዳ የምታደርግ ጥሩ መጽሐፍ ናት። ሁላችንም እንደምናውቀው የፈጣሪያችን ስም በመጀመሪያ የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ስለሆነ ይህች መጽሐፍ የስሙን ትክክለኛ ትርጉም ለማወቅ የምትጠቅም በአይነቷ የመጀመሪያ የሆነች ግሩም መጽሐፍ ናት። በኤሎሂም ፈቃድ እስራኤል አገር የምኖር የዕብራይስጥ ቋንቋ ተናጋሪና የጌታ አገልጋይ እንደመሆኔ መጠን የመጽሀፏን ጠቃሚነት በግልፅ ተረድቻለሁ። ይህን መጽሐፍ የሚያነብ ሁሉ ጥልቅ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እንደሚያገኝ እርግጥኛ ነኝ። በተለይም የቃሉ አገልጋዮች የሆን ሁሉ፤ ለአገልግሎታችን መሳካት ታላቅ አስተዋፅዖ ያላት ድንቅ መጽሀፍ ስለሆነች፣ ሁላችሁም እንድታነቧት አበረታታለሁ። ይህን መጽሀፍ በብዙ መስዋዕትነት አዘጋጅቶ ያቀረበልንን ፓስተር ኮከብን ጌታ ይባርክህ ለማለት እወዳለሁ።

"በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ።" (መዝ.91፥14) የእስራኤል አምላክ ከፅዮን ይባርካችሁ!

ቤኒ ሞገስ
የቁጥቋጦው እሳት ጉባዔ ፓስተር
ሐይፋ እስራኤል

"የኤሎሂምን ስም" ማወቅ ለሕይወታችን ታላቅ አስተዋጽዖ አለው። ዳንኤል 11፥32 ላይ " ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም" ይላል። በዚህ ክፉ ዘመን በታማኝነት መቆም የሚያስችለንን አምላካችንን ማወቂያ፤ ብሉም

"ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥
ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ
ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና
እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥
የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን
ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥
የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ
ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ
እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን
ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።"
ራእይ 15: 3-4

# የፈጣሪ ስሞች
# (שם האלוהים)

ኮከብ ገዳሙ

HOUSE OF ISRAEL
INTERNATIONAL MINISTRIES, INC
P.O.BOX 461262
AURORA, CO 80046
USA
www.hoisrael.org
hoisrael@hotmail.com
kogedamu@gmail.com
720-987-9951

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

መግቢያ

1. የፈጣሪያችን ማንነት ........ 1

2. ቅዱስ ስሙን እንወቅ
   2.1 የስም አስፈላጊነት ........ 9
   2.2 የአምላክን ስም ማወቁ ለምን አስፈለገ? ........ 11
   2.3 የተገለጠባቸው መሠረታዊ ስሞች ........ 13
   2.4 የስሙ ታላቅነት ........ 14

3. የብሉይ ኪዳን ስሞች
   3.1 ኤል ........ 16
   ኤሎሂም ........ 20
   ኤልሻዳይ ........ 22
   ኤልሮኢ ........ 35
   ኤል የላም ........ 39
   ኤል ብሪት ........ 41
   ኤል ጊቦር ........ 45
   ኤል ዔልዮን ........ 49
   3.2 ያህዌ ........ 55
   ያህዌ ያርኤ ........ 61
   ያህዌ ሮፌ ........ 62
   ያህዌ ንሲ ........ 65
   ያህዌ መካዴሽ ........ 67

የሀዋ ፪
ኤል

# ቅዱስ ስሙን እንወቅ

## 2.1 የስም አስፈላጊነት

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በአስራ ዘጠኝ ዘጠና ዓ.ም የመጀመሪያ ልጃችንን ጌታ በካርቱም ከተማ ሱዳን ውስጥ ሲሰጠን ማን እንበላት በሚል እኔና ባለቤቴ ሕይወት የነበረንን ጭንቀት እስታውሳለሁ። ምክንያቱም ልጃችን ከተወለደችበት ጊዜ ጀምራ ምድሯን እስከምትለቅበት ጊዜ ድረስ የምትጠራበትና የምትታወቅበት የማንነቷና የግቧ መድረሻ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ብዙ ተጨንቅን ብዙ ሰዎችንም አማከርን። በመጨረሻም ምሕረት ወይም በዕብራይስጥ (ሩሃማ) ብለን ሰየምናት። ምክንያቱም የተወለደችው የስቅለት ቀን ስለነበረና የጌታን ምሕረት የምናስታውስበትና የተቀበልንበት ቀን ስለነበረ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፍጥረት በሙሉ በየቀኑ ይጠራታል። እርሷም ስሟ መሆኑን ስላወቀች በምትጠራበት ጊዜ ሁሉ ምላሽ ትሰጣለች።

መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ለፍጥረት ሁሉ በመጀመሪያ ስም እንዲያወጣ ሥልጣን የተሰጠው ለመጀመሪያው ሰው ለአዳም ነበር። ዘፍ.2፥18- አዳም በመገለጥና ከጌታ በተቀበለው እውቀት ለእንስሳት ሁሉ ያወጣላቸው ስም ለዘላለም መጠሪያቸው ሆኖ

፫

# የብሉይ ኪዳን ስሞች

## 3.1 ኤል (אל)-Omnipotent-Mighty, Powerful

ኤሎሂም (אלוהים) የሚለውን ከማየታችን በፊት ኤል (אל) የሚለውን የስሙን ሥር ማየቱ በጣም አስፈላጊ ነው። ኤል (אל) የሚለው ቃል የፈጣሪ የነጠላ መጠሪያ ስም ሲሆን ፥ ትርጉሙም ኃይለኛ ጠንካራ ባለ ሙሉ ኃይል የሚለውን አሳብ በመያዝ፥ ፈጣሪ ብቻ ብቻውን አድራጊና የሁሉ መነሻ እንደሆነ የሚያመለክት ነው። በብሉይ ኪዳን ብቻ 250 ጊዜ ተጠቅሷል። በተጨማሪም የመጀመሪያ ጌታና ገዢ መሆኑንም ከስሙ ትርጉም እንረዳለን። ይሁን እንጂ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ኤል (אל) ብቻውን የፈጣሪ መጠሪያ ሆኖ ለብቻው አናየውም። እርግጥ ኤል(אל) የኢሎሂም አጭር መጠሪያው ስሙ በመሆን ከቀጣይ ባህሪው ጋር በመጣመር ይጠራል። ከኤል ጋር የተያያዘውን ስሙ በሰፊው ስለምናጠናው የበለጠ እየገባን ይመጣል።

ለምሳሌ

- በዘፍጥረት 14:20 ላይ በመልከ ጼዴቅና በአብራም ግንኙነት ጊዜ የተጠቀሰው የእምላክ ስም ኤል (אל) ነው።

ፀሐይ ይኖራል። ለዘላለም እንደ ጨረቃ ይጸናል
ምስክርነቱ በሰማይ የታመነ ነው።" ዳዊት 89 ፥ 34-37

ዳዊትም የቃልኪዳኑን ታላቅነት ሲገልጽ በመዝሙር 119 ቁጥር 89-90

"አቤቱ፥ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል። እውነትህ
ለልጅ ልጅ ናት ምድርን መሠረትሃት እርስዋም
ትኖራለች።" ይላል።

ቃልኪዳን በእስራኤላውያንም ሆነ በመካከለኛው ምስራቅ በሚኖሩ ሕዝቦች ዘንድ ታላቅ ቦታ የሚይዝና አብዛኛውን ጊዜ በደም የሚደረግ መሃላ ነው። ደም የሕይወት ምልክት በመሆኑ ከሞት በስተቀር የሚለውጠው ኃይል የለም። ኤሎሂም(אלוהים) ሕዝቡ ደምን እንዳይበላ አዝዟል።

"ከእስራኤልም ልጆች ወይም በመካከላቸው ከሚኖሩ
እንግዶች ማናቸውም ሰው ደም ቢበላ፥ ደም በሚበላው
በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብድበታለሁ፥ ያንንም ሰው
ከሕዝቡ ለይቼ አጠፋዋለሁ። " ዘሌዋውያን 17፥ 10

" ስለዚህ የእስራኤልን ልጆች። ከእናንተ ማንም ደምን
አይበላም፥ በመካከላችሁም ከሚኖሩ እንግዶች ማንም
ደምን አይበላም አልሁ።" ዘሌዋውያን 17፥ 12

"የሥጋ ሁሉ ሕይወትና ደሙ አንድ ነውና ስለዚህ
ለእስራኤል ልጆች። የሥጋ ሁሉ ሕይወት ደሙ ነውና
የሥጋውን ሁሉ ደም አትብሉ የሚበላውም ሁሉ ተለይቶ
ይጥፋ አልኋቸው።" ዘሌዋውያን 17፥ 14

